# የኢትዮጵያ ሕዝባዊ አብዮታዊ ፓርቲ (ኢሕአፓ)

Ethiopian People's Revolutionary Party (EPRP)

መጋቢት 29 ቀን 2004 ዓ.ም

## ከሚያዚያ እስከሚያዚያ 1964-2004
## የኢሕአፓ 40 ያልተቋረጠ ትግል ዓመታት

ኢሕአፓ ሉዓላዊነትና ዴሞክራሲያዊት በሆነች ኢትዮጵያ መላ ሕዝቡ ባለ ሙሉ መብት ሊሆን የሚችልበት ሥርዓት ዕውን ይሁን የሚል ራዕይን ይዞ ከ40 ዓመት በፊት የተቋቋመ ፓርቲ ነው። ሕዝብ ባለ መብትና የሥልጣን ምንጭ ይሁን ከሚል ባደረገው ያልተቋረጠ ትግል ከባድ መስዋዕትነትን ከፍሏል። የሕዝብ ጠላቶች የሚችሉትን ሁሉ የማጥፋት ዘመቻና ይህ ነው የማይባል ጉዳትን ቢያደርሱበትም ከዚህ የማያወላዳ "የሀገር ሉዓላዊነት፣ የዜጎች እኩልነት የተከበረበት የሀገር አንድነት እና የሕዝብ የሥልጣን ምንጭነት ይከበር" በሚለው አቋሙ ፍንክች ሳይል እንደፀና አለ።

ኢሕአፓ በመጋቢት - ሚያዝያ 1964 ዓ.ም በተካሄደ ጉባኤ ሲመሠረት፤ ዴሞክራሲዊት ኢትዮጵያ ዕውን እንድትሆንና  ሕዝባዊ መንግሥት እንዲመሠረት ቃል ገብቶ ነው ትግሉን የጀመረው። ኢሕአፓ ለዴሞክራሲና ለሕግ የበላይነት ያደረገው ትግል አርባ ዓመቱን እነሆ ዘንድሮ አስቆጥሯል። በዚህ ሕዝባዊና ዴሞክራሲያዊ አቋሙም የተፈራረቁት ሶስቱም (የአፄ ኃ/ሥላሴ፣ የመንግስቱ ኃ/ማርያምና ያሁኑ በመለስ የሚመራው ወያኔ) አገዛዞች በሕጋዊ መንገድ፣ በነጻ በሀገሩ እንዳይንቀሳቀስ አርገውታል፣ አግደውታል።

የየካቲት 66-ሉ አብዮት ሲፈነዳ ኢሕአፓ ገና ያልተጠናከረ ስለነበር ሙሉ ለሙሉ የመሪነቱን ቦታ መያዝ ባይችልም፣ ባጭር ጊዜ ውስጥ ግን የሚያስፈልጉትን ድርጅታዊ መረቦችን በመዘርጋት ሕዝብን አስተባብሮ፣ ትግሉን ለማጎልበት  ከፍተኛ ሚናን ተጫውቷል። በመንግሥቱ ኃ/ማርያም ይመራ የነበረው ደርግ የሕዝቡን አብዮት ጠልፎ ሥልጣኑን በቁጥጥሩ ስር ሲያደርግ፤ ኢሕአፓ "ሕዝባዊ የሽግግር መንግሥት ይቋቋም" በሚል መፈክሩና ጥሪው ሥር ከፍተኛ የሕዝብ ተቀባይነትን አግኝቶ ሰፊውን ሕዝብ ለሥልጣን ባለቤትነት በማነሳሳቱ ለትግሉ ሕዝባዊ ይዘትና ጥልቀት ሰጥቶት ነበር። በዚህ ሕዝብን ከዳር እስከዳር ያንቀሳቀሰ የኢሕአፓ የፖለቲካ ሥራ የተደናገጠው ደርግ በሶቭየት ካምፕ ካሉ አጋሮቹ ጋር በመሆን ፓርቲውን ለማጥፋት ነጻ እርምጃና <u>ቀይ ሽብር</u> የተባለውን ለማወጅና አዋጁንም በተግባር ለማዋል ጊዜ አልወሰደበትም። መንግሥቱ ኃ/ማሪያም በመሥቀል አደባባይ "ያናርኪስቶችን (የኢሕአፓን ለማለት ነው) ደም እንዲህ እናፈሳለን" እያለ ጠርሙስ እየሰበረ በፓርቲው ደጋፊዎችና አባላቱ ላይ ያወጀው የቀይ ሽብር የይፋ ዘመቻ፣ ከሩብ ሚሊዮን በላይ ሕይወትን ያረገፈ፣ ቁጥር ሥፍር የሌላቸውን ዜጎች ኑሮ ያፈናቀለ፤ ብዙ ሺዎችን አካለ ስንኩል ያደረገ ነው። እስከጥርሱ የታጠቀው ደርግ በሶቭየትና አጋሮቹ እየታገዘ ጭምር ምንም ይህ ነው የሚባል ትጥቅ በሌለው ኢሕአፓ (ባጠቃላይ ሕዝቡ) ላይ አሰቃቂ የፍጅት ዘመቻውን ያደረገው፤ በፖለቲካው መስክ በሀገሪቱ

EthioLion.Com

ባጠቃላይ ኢሕአፓ ባዶውን አስቀርቶት እንደነበር ስለተገንዘበ መሆኑ የተመዘገበ ብቻ ሳይሆን ዛሬም በሕይወት ያለው ሁሉ የሚመሰክረው ነው።

ኢሕአፓ ባንድ በኩል አምባገነኑን የመንግሥቱን/የደርግን አገዛዝ እስከወደቀበት ግንቦት 1983 ድረስ በትጥቅ ትግል ሲፋለም የነበረ ሲሆን በሌላ በኩል ኢትዮጵያን ለመበታተን የተነሱ ኃይሎች (እንደ ወያኔና ሻዕቢያ ያሉት) ያልተቋረጠ የማጥፋት ዘመቻ (በፓርቲው) ላይ አካሂደውበታል። የደርግ አገዛዝ በማክተሚያው ወቅትም ዛሬ ሀገራችንን መቀመቅ ውስጥ እየከተተ ያለው ጠባቡ ቡድን ወያኔ፣ ወደመሀል ሲገሰግስ በሱዳንና ሻዕቢያ እየታገዘ በቅድሚያ ኢሕአፓን የማጥፋት ዘመቻውን አካሂዷል። ኢሕአፓ ግን ይህ ሁሉ ከግራ ከቀኝ ከጠባብ፣ ከባዕድ ያልተቋረጠ ዘመቻ ሲደረግበት የዛሬ አርባ ዓመት በፊት ይዞት የተነሳውን ዓላማ ሳይሸጥ፣ ላንዴም ፍንክች ሳይል ቀጥሏል።

ድርጅቱ የያዘውን ዓላማ በማናቸውም ሕጋዊ መንገድ በሰላም ተግባራዊ ለማድረግ በነበሩት መንግሥታት ሁሉ አሁን ያለውን ወያኔ ጨምሮ በመከልከሉ በሀገር ውስጥ በህቡዕ በመደራጀትና በመንቀሳቀስ እንዲሁም በውጭ ሀገሮች በይፋ ሳያቋርጥ በልዩ ልዩ መንገድ ትግሎችን አካሂዷል፤ እያካሄደም ነው። አባላቱን ማሳደዱ ዛሬም አልቆመም። በስደት ካሉበት የጎረቤት ሀገራት ሳይቀር ብዙ እንግልትና መከራ ይደርስባቸዋል፤ ለወያኔ አሳልፎ የተሰጡም አሉ። የመለስ አገዛዝ ኢሕአፓን የሚመለከት እራሱን የቻለ የመረጃ ክፍል አቋቁሞም የኢሕአፓን አባላት ለማሳደድ፣ ድርጅቱንም ለማጥፋት በሚችለው ሁሉ እየተረባረበ ይገኛል።

ኢሕአፓ ግን ለዚህ ሁሉ ሳይበገር ትግሉን ቀጥሏል። ዛሬም በፍኖተ ዴሞክራሲ ሬዲዮው አማካይነት ድምፅ ለሌለው ሕዝብ ድምፅ ሁኖ ካሥር ዓመት በላይ ጠባቡን ወያኔ በማጋለጥ፤ በመላ ሀገሪቱም ልዩ ልዩ ሕዋሳትን በህቡዕ በመፍጠር የሚጠይቀውን መስዋዕትነት በመክፈል ይታገላል። ለህብረት ትግል ከቀድሞ ጀምሮ ባለው ከፍተኛ ዕምነት በተለያየ ጊዜ ከሌሎች ኢትዮጵያውያን ኃይሎች ጋር በመሆን ህብረትን (ለምሳሌ እንደ ኢዴሐቅና ኢዴኃህ ያሉትን) በመፍጠር ታግሏል። በህብረተሰብ ውስጥ ልዩ ልዩ የሕብረተሰብ ክፍሎች - ሴቶች፣ ወጣቶች፣ ሠራተኞች፣ መምህራን፣ አርሶ አደሮች፣ ጋዜጠኞች... ወዘተ - በነጻ ተደራጅተው ለመብታቸው መታገል አለባቸው፤ ከፖለቲካ ኃይላትም የሚቻለው ትብብር ሁሉ ሊደረግላቸው ይገባል ከሚለው ዕምነቱ በመነሳት ባሳለፋቸው የትግል ዓመታት ሁሉ ይህንን ሲያደርግ ቆይቷል ፤ ዛሬም እያደረገ ነው።

ያሳለፈው የ40 ዓመታት የትግል ጉዞ አልጋ ባልጋ እንዳልነበር ሁሉም የሚያውቀው ነው። በትግሉ ሂደት አብረውት እስከዛሬም የቀጠሉ ያስቀጠሉ እንዳሉ ሁሉ ያልቀጠሉ፣ ጉዳት አድርሰው የከዱና ሊበታትኑትም የጣሩ እንደነበሩ የምናስታውሰው ነው። ትግል መራራና ብዙ ውጣ ውረድ የመላበት ቢሆንም "ትግል ሲመር ይጥመናል"፤ "መራራው ትግል ቀጥሏል" -ን እየዘመሩ "የትግሉ ነው ሕይወቴ" ባሉት ጀግኖች ልዩ ልዩ መስዋዕትነት ዛሬም ኢሕአፓ፤ አንገቱን ቀና አርጎ ሳይሸማቀቅ ቀጥ ብሎ ይሄዳል። ወጣቱ በድርጅቱ ወክንድ



EPRP
P.O.Box 73337
Washington DC, 20056
USA
Tel. 202-291-4217 Fax 202-291-7645

E-mail : ESPIC@aol.com

Website: www.EPRP.com

EPRP
BP 22
Bois colombes 92270
France

አማካይነት የትግሉን አርማ ተረክቦ ወደፊት ትግሉን ለማስቀጠል ቃል ገብቷል፤ በሀገርና ከሀገርም ውጭ በመታገል ላይ ይገኛል።

አርባ የትግል ዓመቱን የምናነሳው እንዲያው ለማንሳቱና ለቁጥሩ ሳይሆን በነዚህ ዓመታት በትግሉ የወደቁት፣ የአዕምሮና የአካል ጉዳት የደረሰባቸው፣ የተሰደዱት ሁሉ የከፈሉት መሥዋዕትነትን ለመዘከር ነው። የመጨረሻ ዓላማቸው ዛሬም ግቡን አለመምታቱን አበክረን በማስታወስ ትግሉም መቀጠል እንዳለበት ልብ እንዲባል ስለምንፈልግ ነው። ይህን ሁሉ መስዋዕትነት መክፈላቸው ላንድና አንድ ዓላማ ብቻ ነው ብሎ ያምናል ኢሕአፓ - ሕዝቡን የሥልጣን ምንጭ በማረግ የሥልጣኑ ባለቤት የሚሆንባት ሉዓላዊትና ዴሞክራሲያዊት ኢትዮጵያን ዕውን ማረግ ! ኢሕአፓ ለመስዋዕትነታቸው ክብር የሚሰጠው፤ ይህ ዓላማቸው ሳይዛነፍ ግቡን እንዲመታ ትግሉን ለመቀጠል አሁንም ቃል በመግባት ነው።

ትግሉ ይቀጥላል!
ድል ለኢትዮጵያ ሕዝብ!!
እናቸንፋለን !!!

EthioLion.Com



EPRP
P.O.Box 73337
Washington DC, 20056
USA
Tel. 202-291-4217 Fax 202-291-7645

E-mail : ESPIC@aol.com
Website: www.EPRP.com

EPRP
BP 22
Bois colombes 92270
France